# Muslimah Who Taught Their Husbands

# ባሎቻቸውን ያስተማሩ ሙስሊም ሴቶች



ትርጉም በወጣቱ ተልዕኮ(አህመድ የሱፍ)

## Presented by: Youth-Mission Online Amharic Islamic Books Publishing.

# Muslimah Who Taught Their Husbands

## ባሎቻቸውን ያስተማሩ ሙስሊም ሴቶች

**በቢንቱ ሰቢል**

**ትርጉም በአህመድ የሱፍ**

All right reserved

**© የወጣቱ ተልዕኮ**

**የወጣቱ ተልዕኮ ኦንላይን እትም 2008**

**ሰሜን ወሎ ወልዲያ**

**ahmedyesuf29@gmail.com**

**+251927790323**

**http://youth-mission.mobie.in**

አላዋቂ ሙስሊሞችም ሆኑ ሙስሊም ያልሆኑ የሴት መብት ጠበቆች ሙስሊም ሴቶች ጭቁኖች ፣ ኋላ ቀር ፣ በኢስላም ቦታ የሌላቸው አድርገው ያስባሉ።

የሴትን ልጅ ህይወት ከጨለማው ዘመን ያላቀቀ ፣ ሴቶች ከወንዶች ጋር ጦርሜዳ እንዲዘምቱ የፈቀደ ፣ እኩል ከወንዶች ጋር ሐዲሶችን እንዲያስተላልፉ ያደረገ ኢስላም እንደሆነ ቢያውቁስ። ህዝባቸውን ፣ ባላቸውን ፣ ልጆቻቸውን በማስተማር ይህን ትውልድ የቀረፁ ሴቶች እንዳሉ ቢረዱስ።

# ባሎቻቸውን ያስተማሩ ሙስሊም ሴቶች

## በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

**በቢንቱ ሰቢል**

**ትርጉም በአህመድ የሱፍ**

አይናችሁ እዚህ ርዕስ ላይ እንዳረፈ የመደመም የመገረም ስሜትና ምናልባት ባሎቻቸውን ያስተማሩ ሙስሊም ሴቶች ይኖሩ ይሆን የሚል ጥያቄ በህሊናችሁ እንዳቃጨለ ይሰማኛል። ይህ የመገረም ስሜት የተፈጠረው በዚህ ዘመን ያለን የኡመተ ሙሐመድ ህዝቦች ወንዱም ሴቱም የእውቀት ድሃ በመሆኑና ለጅህልና እጅ የሰጠን በመሆኑ ምክኒያት ነው።

ባሁኑ ወቅት ሙስሊም ሴቶች ባሎቻቸውን ላያስተምሩ የሚችሉባቸው በርካታ ምክኒያቶች አሉ። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1ኛ ባሎቻቸውን የሚያስተምሩበት እውቀት የሌላቸው በመሆኑ

2ኛ ሚስቴ እኔን ማስተማሯ ያሳፍረኛል በማለት ባል ከሚስቱ መማር ባለመፈለጉ

3ኛ ባልና ሚስት ቁጭ ብለው ስለሃይማኖታቸው የሚማማሩበት ጊዜ የሌላቸው በመሆኑ

4ኛ አንዳቸው ወይም ሁለታቸውም ኢስላምን የማጥናትና የመማር ፍላጎት የሌላቸው በመሆኑ ነው።

ቀደምት ሙስሊሞች ግን ከዛሬ ሙሊሞች በጣም የተለዩ ብርቅየ ነበሩ። ለዲነል ኢስላም እውቀት በነበራቸው ፍቅር ምክኒያት ባልና ሚስት አንድ ላይ ቁጭ ብለው የሚማማሩበት ጊዜ ነበራቸው። ምክኒያቱም ቀደምት ኡለማዎች አንዲት የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ በመፈለግ ለወር ያህል ይጎዙ እንደነበር ያውቃሉና። ሆኖም እነዚህ ሰዎች አሊም ሚስቶቻቸው የአሏህ

ትልቅ ችሮታ እንደሆኑ የሚቆጥሩ ሲሆን የኩራታቸውና የክብራቸውም ምንጭ ነበሩ።

ዛሬ ግን አይደለም ሚስት ባሏን  የምታስተምርበት ጊዜ ይቅርና የቤት ውስጥ ችግሮቻቸውን በውይይት የሚፈቱበት ጊዜ እንኳ ያጡ እስኪመስል ድረስ ፍቹ በርክቷል። በሚያሳዝን ሀኔታ የኢስላም ኡለማዎች ወንዶች ብቻ እንደሆኑ ተደርጎውም እየተቆጠረ ይገኛል። ሰውም ከእውቀት ይልቅ አሉቧልታ ፣ ጨዋታ ፣ እንቶፈንቶ ወሬ እየመረጠ አለም ተገላብጣ ዳግም ድንቁርና(ጅህልና) እየተስፋፋ ይገኛል። የሴት መብት ተሟጋቾች ዛሬም ኢስላም የወንዶች ሃሳብና አስተያየት ብቻ ሆኖ እናገኘዋለንና የአሏህ ቃል ፣ የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ እና የኢስላም ህግጋት በሙሉ እንደገና ሊብራራ ይገባል ሲሉ መልካም የሚመስል መርዛማ አመለካከቶችን እየረጩ ይገኛሉ።

- ከሚስት መማር ያሳፍራል ብላችሁ የምታምኑ
- እውቀት በማስፋፋት ረገድ ሙስሊም ሴቶች ሚና የላቸውም የምትሉ
- ሚስቴ እንዴት ታስተምረኛለች የሚል የእብሪተኝነት ስሜት የወጠራችሁ
- አሊምነትን የወንዶች ብቻ አድርጋችሁ የምታስቡ
- የኢስላም ህግጋቶች መቀየርና እንደገና መብራራት እንዳለባቸው የምትከራከሩ የሴቶች መብት ጠበቆች

ይችን አነስተኛ ጽሑፍ አንብቧት!

## ፋጢማ ቢንት አል-ሙንዚር ኢብን ዙበይር ኢብን አል-አዋም

አስማ(ረ.ዐ) በኢስላም ታሪክ ውስጥ በደምብ የምትታወቅ የምንጊዜም ተምሳሌት ናት። አስማ የአቡ በክር(ረ.ዐ) ልጅ ፣ የአኢሻ(ረ.ዐ) እህትና የዙበይር ኢብን አል-አዋም ሚስት ነበረች። ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በመርዳት የነበራት ሚና ፣ የመስዋዕት ምሳሌነቷ ትዕግስቷና ፅናቷ በኢስላም

ዘላለም ሲወሳ ይኖራል። ዛት ኒትቀይን (የሁለት መቀነቶች ባለቤት) ተብላ ትጠራለች። ይህን መጠሪያ ያገኘችው ለነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እና ለአባቷ አቡ በክር(ረ.ዐ) በመቀነቷ ምግብ ቋጥራ በድብቅ ይዛላቸው የምትሄድበት አጋጣሚ ስለነበር ነው።

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እና አባቷ አቡ በክር(ረ.ዐ) ከመካ ወጥተው ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ ጠላቶቻቸው ያሳድዷቸው ጀመር። እነሱም ለተወሰነ ጊዜ ተደብቀው ቆዩ። አስማ(ረ.ዐ) ህይወታቸውን ከጠላቶቻቸው ሴራ ለመታደግ በእርግዝና ጊዜዋ የሰውርን ተራራ ወጥታ በሚስጥር ምግብ ማቀበሏን ስራዋ አደረገችው። ይህን ተራራ ለማታውቁ አለታማ መንገዱን ወጣቶች ሲወጡ የሚያቃስቱ መሆኑን ማወቁ ይበቃችኋል። አስማ(ረ.ዐ) ከማህፀኗ ካለው ልጇ ጋር እንዲህ ያለ ፈታኝና አስቸጋሪ ጉዞን እንድትጎዝ ያደረጋት ለነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እና ለአባቷ ከነበራት ጥልቅ ፍቅር በላይ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?


አንድ ወቅት አቡ ጀህል እሳት ለብሶ ጎርሶ ወደ አቡ በክር ቤት መጣና አስማን ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እና አባቷ አቡ በክር የሚገኙበትን ቦታ ጠየቃት። እሷም በኢማን ቆፍጠን ብላ ቆማ አላውቅም ስትል መለሰችለት። ፊቷን በጥፊ መታት። እሷ ግን ልቧ በዲነል ኢስላም ፍቅር ተሞልቶ ሳትበገር ዳግም ቆፍጠን ብላ ቆመች። ይህ ፍቅሯ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሞት ብኋላ እንኳ አላበቃም። ይልቁንም ፍቅሯን በልጆቿና በልጅ ልጆቿ ልብ ውስጥ አቀጣጠለችው። እሷን በመኻደሚ በጣም የተጠቀመችው አንዷ የልጅልጅ ፋጢማ ቢንት አል-ሙንዚር ናት። አሷህ ስሟን በሐዲስ መጽሐፎች ውስጥ እንዲወሳ መርጧታል።

ፋጢማ ቢንት አል-ሙንዚር በጊዜዋ የተከበረች ከመሪ ታቢአት አንዷ ናት። ታላቅ አሊም የነበረች ሲሆን በፋቂህነቷ (በህግ አዋቂነቷ) ትታወቃለች። ባሏ የአጎቷ ልጅ የሆነው ሒሻም ቢን ኡርዋ ኢብን አል-ዙበይር ይባላል። ሒሻም ታላቅ አሊምና ዘጋቢ ነው። ከታዋቂ ተማሪዎቹ መካከል ኢማሙ አቡ ሐኒፋ ፣ ኢማሙ ማሊክ ፣ ሱፍያኑ ሰውሪ ይገኙበታል።

ምንም እንኳ የአጎት ልጅ ቢሆኑም ፋጢማ ከአስማ(ረ.ዐ) ያገኘችውን የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ብዙ ሐዲሶች አላገኘም። ሆኖም ከሚስቱ የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ንግግር በመጠየቅና በመማር ሸምድዶ ጎዶቹንና ተማሪዎቹን ያስተምራል። ብዙዎችም ከፋጢማ ይዘው ዘግበዋል። ለምሳሌ በጣም ታዋቂ የሲራ መጽሐፍ ያዘጋጀው ሙሐመድ ኢብን ኢስሐቅ ፣ ባሏ ሒሻም እና ሌሎችም

ከፋጢማ ይዘው ዘግበዋል።

ከታች የተጠቀሱት ሐዲሶች ሒሻም ከሚስቱ ከፋጢማ ተምሮና ፋጢማ ደግሞ ከአስማ ተምራ ያስተላለፈቻቸው ለመሆኑ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው።




1. ሒሻም ከፋጢማ ይዞ እንዳስተላለፈው አስማ(ረ.ዐ) "አንዲት ሴት ወደ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) መጣችና የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ! ሙሽራ የሆነች ልጅ አለችኝ። ፀጉሯን የሚያሳሳ በሽታ (ሃስባ) አለባት። ሌላ ፀጉር ከፀጉሯ መቀጠል እችላለሁን? አለቻቸው። የአሏህ መልዕክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) የአምላክ እርግማን (ዊግ) በቀጣዩና እንዲቀጠልለት በሚጠይቀው (በአስቀጣዩ) ላይ ነው ብለዋል" ብላለች።

   ይህ ሐዲስ በቡኻሪ ፣ በሙስሊም ፣ በነሳኢ ፣ በኢብን ማጃ ተዘግቧል።

2. ሒሻም እንዲህ አለ ፋጢማ ከአስማ ይዛ እንዳስተላለፈችው አስማ ከፈረሶቻችን የአንዱን ስጋ በነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ በልተናል ብላለች።

   ይህ ሐዲስ በቡኻሪ ፣ በሙስሊም ፣ በነሳኢ ፣ በኢብን ማጃ ተዘግቧል።

3. ሒሻም ከሚስቱ ከፋጢማ ይዞ እንዳስተላለፈው አስማ(ረ.ዐ) የአሏህ መልእክተኛ(ሰ.ዐ.ወ) (ከሃብትሽ) ስጭ ፣ ከእሱም አውጭ ከፈይ ከእሱ ጋር አትጣበቂ (አጥብቀሽ አትያዥ)። ያለበለዚያ አሏህ በአንች ላይ ይይዝብሻል፤ አትቁጠሪ አሏህ ባንች ላይ ይቆጥርብሻልና ብለውኛል ብላለች።

   ሐዲሱ በቡኻሪ ፣ በሙስሊም ፣ በነሳኢ ተዘግቧል።

ታዋቂ ከሆኑ ኡለማዎች መካከል ልክ እንደ ቡኻሪና ሙስሊም ያሉ ይች ታላቅ ሴት ያስተላለፈችውን ሐዲስ ወይም ባል ከሚስቱ ተምሮ ያስተላለፈውን ሐዲስ ዘግበዋል።

ታዲያ ይህ የኢስላም ኡለማዎች ወንዶች ብቻ እንደሆኑ ለሚያስቡና ሴቶች በኢስላም ቦታ እንደሌላቸው ለሚዶልቱ ትልቅ ትምህርት ይዟል። በተቃራኒው ትክክለኛ የኢስላም እውቀት ምንጭ የሆኑት መጽሐፎች ሴቶች ያስተላለፏቸውን ሐዲሶችና በሐዲስ ዘገባ ሰንሰለት ላይ ስማቸው የሚጠቀስ ሙስሊም ሴቶች ተመዝግበውበታል። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ምሳሌዎች ባሎች ከሚስታቸው የተማሯቸውን ሐዲሶች ያለምንም እፍረት በግልፅ ማስተላለፋቸው በቂ ማስረጃዎች ናቸው። እነዚህን ሐዲሶች ሒሻም ከሚስቱ ከፋጢማ ፋጢማ ደግሞ ከአስማ ተምራ ባይሆን ኖሮ ይህን የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) እፁብ ድንቅ ጥበብ ባላገኘነው ነበር!

## የሰኢድ ቢን አል-ሙሰይብ ልጅ

አቡ ኹረይራ(ረ.ዐ) ሴት ልጁን ለታዋቂው ታቢኢ ሰኢድ ቢን አል-ሙሰይብ ዳራት። ከዚህ ከተባረከ ትዳር አሏህ አሊምና ተቅይ ሴት ልጅ ሰጣቸው። ልጁም ለትዳር በደረሰች ጊዜ ሰኢድ ኢብን አል-ሙሰይብ ከተማሪዎቹ መካከል አብዱሏህ ተብሎ የሚጠራ ተማሪውን የትዳር አጋሯ እንዲሆን መረጠላት።

አብዱሏህ ለእውቀት ጥልቅ ፍቅር ስለነበረው የጫጉላ ጊዜውን እንኳ ሳይጨርስ በተዳረ በሁለተኛው ቀን ካባውን ለብሶ ሊወጣ ሲል ሙሽራው ወዴት ነው የምትሄደው? ስትል ጠየቀችው። እሱም እውቀት ለመቅሰም ወደ ሰኢድ ጀመአ አላት። እሷም እዚህው ተቀመጥ የሰኢድን እውቀት እኔ አስተምርሃለሁ አለችው።

ይች ቆንጆ ወጣት ልጅ ከአባቷ የተማረችው እውቀት በቂ ስለነበር ከእውቀቷ አስተማረችው። በዚህም ምክኒያት ለአንድ ወር ያክል ከሰይድ ቢን ሙሰይብ ስብስብ (ጀመአ) ላይ አልተካፈለም ነበር።

ዛሬ ላይ ሙስሊም ሴቶች እንዲህ አይነት እውቀት ከባሎቻቸው በላይ ቢኖራቸው ለባሎቻቸው ያላቸውን ክብርና ታዛዥነት ይጨምርላቸው ነበር ወይስ የትዳር ችግር ምንጭ ይሆን ነበር? እስኪ ይህን ጥያቄ ለተወሰነ ደቂቃ ያክል ቆም ብለን እናስብበት። የነዚህ ሴቶች ታላቅነት ግን እውቀታቸው ለባላቸው ታዛዥነትን እና አክብሮትን የሚጨምርላቸው ነበር።

ባል ከሚስቱ እውቀትና ታዛዥነት ያገኘውን ፍቅር ሲናገር "ከቆንጆዎች መካከል ነበረች። በቀልባቸው የአሏህን መጽሐፍ የሚያውቁ ሰዎች ሊቅ ፣ የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሱና አዋቂ እና የባልን ሐቅ ጠንቅቃ የምታውቅ ነበረች" ብሏል።

እናቶቻችን ፣ እህቶቻችን እና ሴት ልጆቻችን በባሎቻቸው አይን እንዲህ አይነቱን ደረጃና ክብር በእውቀታቸው ፣ በታዛዥነታቸው ፣ በዲናቸው ፍቅር የሚጎናፀፍ አሏህ ያድርግልን። አሚን!

## ፋጢማ ቢንት ሙሐመድ ቢን አህመድ

ፋጢማ በጊዜዋ አንዷ ታላቅ ፋቂሐህ (የኢስላም ህግ አዋቂ) ነበረች። በሐነፊያ ፊቅህ ጥልቅ እውቀቷ የምትታወቅ ሲሆን የታላቁ አሊም ሙሐመድ ኢብን አህመድ ኢብን አቡ አህመድ ልጅ ናት። ይህ ሰው ጡህፈቱል ፉቀሃ በሚለው መጽሐፉ በኡለማዎችና በእውቀት ፈላጊ ተማሪዎች ዘንድ በደንብ ይታወቃል። ታዲያ ከአባቷ የተማረችው ፊቅህ ብቻ ሳይሆን ጡህፈቱል ፉቀሃን ጭምር ሸምድዳለች።

ህግ አዋቂ መሆን በራሱ ቀላል ነገር አይደለም። የቁርአን አያዎችን ፣ ሐዲሶችን እና ህግጋታቸውን መሰረት የሚያደርጉበትን የመዝሃብ መርሆዎች በደንብ ማወቅ ይፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ ሁኔታዎችን ወይም አጋጣሚዎችን እና ወቅታዊ ጉዳዮችን ማወቅ ያስፈልጋል። ታዲያ እውቀቷ ከባሏ እውቀት በላይ ስለነበረ የእሷ ምልከታ ወይም ፈትዋ ምን እንደሆነ ያማክራት ነበር። በተለይ ደግም ፈትዋ ሲሰጥ በተሳሳተ ጊዜ። አባቷ አላዲን አቡ

በክር ኢብን መስኡድ አል-ከስአኒ ለተባለ ሰው ዳራት። ይህ ሰው በኡሱል እና በአል ፋር እውቀቱ ይታወቃል። እሱም ለጡህፈቱል ፉቅሃ በዳኢ አል-ሰናኢ በሚል ርዕስ ማብራሪያውን ፅፎ ለሸኹ (ለአባቷ) አሳየ። አባቷ በወቅቱ የነበሩ የባዛንታይን ንጉሶች ያቀረቡላትን የጋብቻ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ አብዱሏህ የፃፈውን የጡህፈቱል ፍቅሃን ማብራሪያ የልጁ መህር(ጥሎሽ) አድርጎ ተቀበለው። በጊዜው የነበሩ ፍቀሃዎችም ይህንኑ መስክረዋል።

ከጋብቻዋ በፊት ከአባቷ ጋር ሆና ፈትዋ ትሰጥ የነበረ ሲሆን ፈትዋዎቹንም ትፅፍ የነበርው እሷ ናት። ካገባችም ብኋላ የአባቷን እና የባሏን ፈትዋዎች ትፅፍ ነበር። ባሏ ሲሳሳትም ታስተካክለው ነበር። ልጃቸው "የሐነፊ መዝሃብን በደንብ ትጠቅስ ነበር። ባሏ አልከሳኒ እንዳንዴ ጥርጣሬና ስህተት በፈትዋዎቹ ውስጥ ስለነበረው ትክክለኛውን አስተያየት ትነግረውና ለስህተቱ ምክኒያቱን ታብራራለት ነበር" ብሏል።

## መርየም ቢንት ጀዕሽ

መርየም ቢንት ጀዕሽ በአራተኛው መቶ ክለፍ ዘመን የኖረች የፊቅህ ፣ የሐዲስ ፣ የተፍሲር እና በሌሎች የኢስላም የዕውቀት ዘርፎች ላይ የላቀች አሊም ስትሆን አሏህ ቁርአንን በገፀበት ቋንቋም ምራቋን የዋጠች ናት።

ጀማል ኢብን አሊ ኢብን አቢ አልፈዋሪስ ለተባለ ታላቅ የየመን አሊም የተዳረች ስትሆን በአረብኛ ቋንቋ እውቀቷ ብቻ ሳይሆን ለባሏ አስቸጋሪ ነጥቦችን በመፍታት በነበራት ፈጣን እና የሰላ አዕምሯዋ ትታወቃለች።

አንድ ወቅት ባሏ ሙርጅዕ ተብሎ ከሚጠራ ፊርቃ ተከታይ ጋር ክርክር ውስጥ ገባ። እነዚህ አፈንጋጮች አንድ ሰው በመገጣጠሚያዎቹ (በአካሉ) የሰራውኝ ስራ ቢሰራ ነጃ ለመውጣት(ለመዳን) ኢማን በራሱ ይበቃዋል ብለው የሚያምኑ ናቸው። ባሏ አሊ በክርክሩ ውስጥ ሱረቱል አዕራፍ አንቀፅ አርባን ጠቀሰ።

**=<({አል-ቁርአን 7፡40})>=**

**{40} እነዚያ አንቀፆቻችነን ያስተባበሉ ከእሷ የኮሩ ለእነሱ የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላቸውም። ግመል በመርፌ ቀዳዳ እስኪያልፍ ድረድ ገነት አይገቡም። እንዲሁ አጋሪዎችን እንቀጣለን።**

ሲከራከር የነበረው ሙርጅአ "ይህ እኮ ለፈጣሪ ቀላል ነው። እሱ ከፈለገ በሃይሉ ግመል በመርፌ አይን እንድታልፍ ያደርጋል" አለ። አሊ ግራ ተጋብቶ ህሊናው በሃሳብ ተውጦ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ሌሊት ላይ እንቅልፍ አልወስድ አለው። ሚስቱ መርየም ችግሩ ምንድነው? ስትል ጠየቀችው። ጉዳዩን ካብራራላት ቡኋላ አሊ ጥሩ ምሽት ብቻ ሳይሆን በጣም ጥሩ የእንቅልፍ ሌሊት የሰጠውን ነገር ነገረችው። እሷም በዚህ የቁርአን አንቀፅ ግመል የግሱ ባለቤት እንጅ ድርጊት ተቀባይ አይደለም ስትል መለሰችለት።

## ፋጢማ ቢንት የኽያ

ፋጢማ ቢንት የኽያ የዘጠንኛው መቶ ክፍለ ዘመን ታላቅ ሙጅተሂዳህ ነበረች። ሙጅተሂዳህ ማለት የኢስላምን ህግጋት ምንጭ የመረዳት ችሎታ ያለው አሊም ማለት ነው። ይህን የህግ ውሳኔና ምርመራም በዘመኑ የነበረውንና በማህበረሰቡ የነበረውን ፍላጎት በመመልከት በወቅታዊ ጉዳዬች ላይ ፍርድ ያስተላልፉበት ነበር። ይህን ሙጅተሂዳህ የሚል መጠሪያ ለመስጠት የግዴታ ሱሃቦች ፣ ወራሾቻቸውና የፊቅህ አሊሞች እንዲሁም ሙጅተሂዶች በተስማሙበትንና በተለያዩበት ሃሳብ ላይ እውቀ ያለው መሆን ግድ ይላል። የሆነሆኖ ሙጅተሂዳ መሆን ቀላል ነገር አይደለም።

አባቷ ህግ አዋቂና ብዙ ተማሪዎች ያሉት ቢሆንም የተለያዩ የህግ ጉዳዮችን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃት ነበር። ይህን ያክል ነበር እውቀቷ። ታላቁ አሊም ሸውካኒ ስለ እሷ ሲናገሩ "በእውቀቷ የመጠቀች ናት" ብለዋል።

አባቷ አል-ሙተኸር ቢን ሙሐመድ ኢብን ሱለይማን ኢብን ሙሐመድ ለተባለ አሊም ዳሯት። ባሏ አሊም ቢሆንም አስቸጋሪና ግራ የሚያጋቡ የፍርድ ጉዳዬች ሲያጋጥሙት ሚስቱን ይጠይቃል። እንዲያውም ከተማሪዎቹ መካከል ሆኖ ውስብስብ ጉዳይ ሲገጥመው ተነስቶ ታላቋ ምጅተሂዳህ ወደ ተቀመጠችበት ከመጋረጃ ጀርባ በመግባት የእሷ ሃሳብ ወይም ፍርድ ምን እንደሆነ ጠይቆ ይመለስ ነበር። መልሱን ይዞ በተመለሰ ጊዜም ተማሪዎቹ ይህ ከአንተ ሣይሆን ከመጋረጃ ጀርባ ካለው ነው ይሉት ነበር።

## አመት አል-ገፉር ቢንት ኢስሃቅ አል-ዲህላዊ

የጨረሻዋ ምሳሌያችን የ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አረብ ያልሆነችው ታላቋ ሙሐዲሳ የሆነችው አመት አልገፉር ቢንት ኢስሃቅ አል ዲህላዊ ናት። አረብ ያልሆነች የተባለበት ምክያት ከላይ የተጠቀሱት አረቦች ስለሆኑና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አረብኛ ስለሆነ ነው የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በህሊናችን እንዳያቃጭል ነው። ይልቁንም ብዙ ታላላቅ አሊሞች ከወንዶች ልክ እንደ ኢማሙ ቡኻሪ ያሉት ከአረብ ዘር አልነበሩም። ልክ እንዲሁ ሙሐዲሳ አመት አል ገፉር ቢንት ኢስሃቅ አል ዲህላዊ ከህንድ ነበረች።

አባቷ ከህንድ አሊሞች መካከል አንዱ ስመጥር አሊም ሲሆን ልጁን ብዙ የሐዲስና የፊቅህ መጽሐፎችን አስተምሮ አሳድጎታል። ሆኖም የሐዲስና የፊቅህ ሊቅ ሆነች። በዚህ መልኩ የሐዲስና የፊቅህ እውቀቷ ከአባቷ እየተማረች ካደገች ብኋላ አባቷ ለአንድ የህንድ አሊም ዳራት። ባሏም ችግር ሲገጥመው ወደ ሚስቱ በመመለስ የሚስቱ መፍትሄ ምን እንደሆነ ይጠይቅ ነበር። አል-ሐሰኒ ይህንኑ ሲያረጋግጡ "ባሏ እራሱ አሊም ቢሆንም በሐዲስ ወይም በፊቅህ ችግር ሲገጥመው ሚስቱን በማማከር ከእሷ ይጠቀም ነበር" ሲሉ ተናግረዋል።

ውድ እህቶቼ ሆይ! ይህን የቀደምት እናቶቻችነን ቅርስ ለመመለስ ዳግም ኢስላም ያብብ ዘንድ ከባሎቻችን ጋር እውቀትን በመሻት እንሽቀዳደም! አሏሁ አዘወጀል በሱረቱል ማኢዳ አንቀፅ 48 ላይ "እርስ በእርሳችሁ በመልካም ስራ ተሽቀዳደሙ" እንዳለው ማለት ነው።

ማንኛውም አይነት አስተያየት ፣ ትችትና ነቀፌታ ካለዎት በኢሜል አድራሻየ ahmedyesuf29@gmail.com ላይ ሊፅፍልኝ ወይም ደግሞ 251927790323 ላይ ሊደወሉልኝ ይችላሉ። የወጣቱ ተልዕኮ ኢስላማዊ መጣጥፎችን ለማግኘት http://youth-mission.mobie.in ይጎብኙ። ጀዛኩሙለህ ኸይረን ከሲረን!